# <u>የእንጦጦ መምህር፤ የሀበሻ ቴክሶችና የጣዖት ጠራቢዎች</u>

ሀማ ቱማ

*“ለውጥ ነው ይሉናል የእነሱ ዓላማ*
*እንሰልጥን ይሉናል እንዳንሆን ፋራ*
*ለእኛ ጭልም ያለው የከበደን ነገር*
*የቸገረን ጉዳይ ያለን ቀፈፍ ቀፈፍ*
*ምሁርነት ብሎ፤ ዘመናዊ ብሎ ፤ እንሰልጥን ብሎ ባንዳነትን ማቀፍ::”*

ወለፈንዲ ይሉታል:: የቃሉን ምንጭ አላውቀውም:: ዛሬ ታፍነው ያሉት ነፃ ጋዜጦች ሲፅፉት የተነበበ ቃል ነው:: ፈረንጆች “ሳታየር” ይሉታል:: የተወሰነ የአፃፃፍ ስልት ነው:: ትችትን በሽሙጥ መልክ ወይም በተራ ሽርደዳ ደረጃ በመወሰን ሳይሆን አለፍ ብሎም ማጋነንም ጨምሮ ግን ሀቅን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ ነው:: ምንም ሆነ  ምን የማንንም ጣዖት አይቀበልም:: አፍራሽ አይደለም ግን የሰው ቅዱሶች ነን ባዮችን ስዩመ እግዚአብሔር ብሎ አይወስድም:: ወለፈንዲ የፖለቲካ መሳሪያ ነው:: ይህን የማይረዱና የሰው ልጆችን በጣዖት ደረጃ የሚያስቀምጡ ግን ለምን “መሪዎቻችን” ተተቹ፤ ይህማ ስድብ ነው ወዘተ በሚል በእኔም ሆነ በሌሎች ላይ ውርጅብኝ ማውረዳቸው አልቀረም:: ሳንሱር በነፍሱ:: ለነገሩ የእነሱ መሪዎች የእኔ ወይም የህዝብ ናቸው ማለትም አይደል:: ገና በጠዋቱ ሳይፈተን ሳይታይ ማንዴላ ጋንዲ ማለቱ ( የሀገራችን አርአያዎች የጠፉ ይመስል) ስለሚደራ፤ሳይገሉ ጎፈሬ ስለሚሰፍን፤ ሀቁን የሚናገር ካለ ክብረ ነክና አፍ እላፊ ተብሎ ውግዘቱ ይጎርፋል:: የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ለዴሞክራሲ የቆሙ ናቸው ስንል ቆይተን መሪዎች ነን የሚሉቱ በአደባባይ ጫማ ያስግሉ መባሉ አልዋጥ ብሎን ጉድ ፈላ ብንልም ጣዖት አምላኪዎቹ ከዚህም ከዚያም ኡኡ አሉ:: ጉሮ ወሸባው ጋር አልገጥም አለ መሰል:: በግል ደረጃ የስድብ መልዕክት የላኩ ጥቂቶች አልነበሩም:: በአፄው ዘመን የጃንሆይ ስም ጠፋ በሚል ዜጎች ቢያንስ ለአምስት ዓመት እስር ይፈረድባቸው ነበር:: የዛሬዎቹ ደግሞ ቅብዓ ቅዱስ ፈሶብናል  ባይሉም ባይታያችሁም ዘውድ ጭነናል ባዮች ሆነዋል መሰል ማን ደፍሮ ይተቸናል የሚሉ ሆኑ:: ግብዝነት በመለስ ዜናዊ ብቻ አልተወሰነም:: ቢያንስ ጭፍሮቻቸውና ጣዖት የጠረቡት ክፍሎች ያሰሙት ኡኡታ ቀላል አልሆነም:: ባዕዳን ጣልቃ ገቦች ስለተተቹ ፀረ ነጭ ህዝብ ሊሉኝ የቃጡ ጥራዝ ነጠቆችም ነበሩ:: ወገንተኝነትምም በሌለበት ተነቦላቸዋል:: በዚህም በዚያም ግን ዝም በል መልዕክቱ ተዥጎድጉዷል:: የሚታፈን ቢኖር!

ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ማለት ሲያንስ ነው:: በበኩሌ ለምን አቅዋምን ግልፅ ማድረጉ እንደሚፈራ አሁንም አይገባኝም:: ከመለስ ጋር መሞዳሞድ ከተፈለገና ከታመነበት ይህንኑ ያዋጣል ብሎ ማቅረብ ተገቢ ነው:: ላመኑበት መከራከር ያስከብራል:: እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር:: ለባዕድ ሽብረክ ማለትም ካለና ከታመነበት ሳይደባበቅ “ጎበዝ አሜሪካ ባዘዘን እንንጎድ” ማለቱ ተቃውሞን ቢያመጣ እንጂ ዋሾ አያሰኝም:: አቅዋምን ደብቆ ህዝብን ለማታለል መቃጣቱ ነው ሀጢያት:: በሰለጠነ ፖለቲካ ሽፋን እጅ እጅ ያለው ቃል ኪዳንን መሻርና ዘመናዊ ባንዳነትን ማቀንቀን ሲከሰት ደግሞ ሀገር ወዳዱ ክፍል ቢቃወም መሳደቡ

የሚያዋጣ አይሆንም:: ቆራጥ ተቃዋሚና ታማኝ ተቃዋሚ ለየቅል ናቸው:: ወንበዴ አገዛዝ በስልጣን ባለበት ታማኝ ተቃዋሚ ሀቀኛ ስሙ ተለጣፊ ነው:: ይህን አላችሁ በሚል ስድብና ውግዘት ቢመጣ አረመኔ አገዛዞችን ስንጋፈጥ የቆየነው እጅ የምንሰጥ አንሆንም:: ሚስተር ቡሽ “ብሪንግ ኢት ኦን” ያለውን ብንጠቅስ ቢገባችወም በእኛው ሀበሺኛ ደግሞ ተንጋጉ እንላቸዋለን:: የህዝባችን ትግል ፍትሃዊና ሀቀኛ ነው ስንል ገና ከጥንስሱ ለሀሰትና ለአድርባይነት አልገዛም ብሎ በባለጌ ስርዓቶች ላይ የተነሳ በመሆኑ ነው:: ጠዋት አብባ ደምቃ በተሰዓት ድፍት እንደምትለውና አረቦች ሰብሀ አልኬይር እንደሚሏት አበባ በታሪክ ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ አለን ለአመፅ ብለው ፀሐይ ደመቅ ስትል ወይም ሁኔታው ሲጣጤስ ወገቤን የሚሉትን የዘመኑን ፖለቲከኞች ማስተናገድ የሰለቻቸው ዜጎች ለሀቅ ቢቆሙና እውነቱን ቢናገሩ መደንገጥ መቆም አለበት:: መባል ያለበት ይባላል፤ መነገር ያለበት ሀቅ ይነገራል:: የሀገራችን የፖለቲካ መድረክ በቃለ አጋኖ አባወራዎች ተጨናንቋል:: ወኔ አጥጦ ምላስ ግን ረዝሟል:: ጠላትና ወዳጅ መለያው አንጎል እንኳን ጠፍቶ ባለበት አንዲያው በደፈናው በእኔ ይሁንባቸሁ፤ ለእኔ ተዉት ዓይነት አዋቂ ምሁር “ልሂቅ” በሉኝ ባዩ በርክቷል:: ታዲያ ይህ ቢነገር ቢጋለጥ ምን ያሰቅቃል?

የኢትዮጵያ ህዝብ በአዲስ አበባ ሼራተን አስረሽ ምቺው የሚለው ወይም ከባዕድ ሀገር ተመልሶ በሕዝብ ላይ የቪዛ ካርድ ከበርቴነቱን የሚያሳየው ሰሞነኛ ወይን ወያኔ መሬት ይመራኛልና አትታገሉት ባዩ አይደለም:: ገዢው ቡድንና ጭፍሮቹ ሕዝብ አይደሉም-- በህዝብ ላይ የተጫኑ አውሬዎች እንጂ:: ለእኔ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አዛውንት ቢሆኑም በጀግንነት ፀንተው ውድ ሀገራቸው መግባት የተከለከሉት እነ ኮሌኔል አስናቀ ዓይነቶቹን አርአያዎችን እንጂ ሚሌኒየም ልጨፍር፤ መሬት ልመራ፤ ቤት ንብረት ላስመልስ፤ ልነግድ ወዘተ እያለ መታወቂያ ከፍሎ ቪዛ ተፈቅዶለት አዲስ አባበ የሚመላሰውን ነገሮች ሁሉ ፅቡቅ ናቸው ባዩን አይደለም:: በዛ? ሰፋ? ወደ ሀገር ሰለገባችሁ ሰልተማላሳችሁ ተወገዛችሁ? ሰለሄዳችሁ ተቀናባችሁ? ይህን ድምዳሜ የሚይዙ ዳግም የነገሮችን ውል ሁሉ መሳታቸውን ያረጋግጣሉ:: ተቃዋሚ ስንልም ከወያኔ ጋር ተቃቅቅፎ የመድብለ ፓርቲን ጭምብል የሚያጠልቀውን የአንድ ጨቋኝ ፓርቲውን ሎሌውን፤ተለጣፊውን አይደለም:: በአዲስ አበባና መቀሌ ከወያኔ መሪዎች ጋር “ጌት ዳውን” ወይም “ደርብ” እያለ ጨፍሮ ዋሺንግተን ወይም ለንደን ተመልሶ ተቃዋሚ በሉኝ የሚለውንም በተመለከተ በማንነቱ ጥያቄ ብናነሳ ተገቢ ነው:: ከኢንተር አፍሪካ ተቋም እስከ የክህደቱ ጎራ ሁሉም ተሰባስበው፤ ራሳቸውን ታማኝ ወይ የሰለጠነ ፖለቲከኛ ብለው አጥምቀው ቢውገረገሩ ህዝብን የሚያደናግሩ አይሆኑም:: ሕዝብ ከዚህ በፊትአመኔታውን እየሰጠ ለአሰመሳዮችና ቃል ኪዳን አፍራሾች ሰለባ ሆኗልና ይህ ስህተቱ እንዲደገም የሚመኝ ሀቀኛ ዜጋ የለም:: ትንሽም ብትሆን ተናግሮ እውነትን ማስከበር ያስፈልጋል:: ላለፈው አንፀፀትም ለሚመጣው አንበለጥም የምንል ከሆነ ደግሞ ካለፈው ስህተት መማርን አንከለከልም ብቻ ሳይሆን አለመማሩ ቅንጦት ይሆናል:: ህዝብ ይመሩናል ብሎ ያመናቸው ለወያኔና ለባዕድ ተሸናፊ ሆነው አስጠቅተውታል:: ዛሬም በአንድ በኩል ለሕዝብ የአንተ ነን እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ ለወዲ ዜናዊና ለቡሽ መንጋ ቡችላ ከሆኑ ሕዝብ ዳግም ሊሞኝላቸው አይገባም:: ስንዴና እንክርዳዱን መለየት ይኖርበታል፤ ከቃላት ባሻገር በገቢርና በተጨባጭ ማን ለሕዝብ ቆሟል፤ማን አሁንም ከመለስ አገዛዝ ጋር ተለሳልሶና ተግባብቶ የአገዛዙን ዕድሜ ወደደም ጠላም ሊያራዝም ተዘጋጅቷል የሚለው መለየት መታወቅ አለበት:: ጉዳዩ የወሳኝ

ትግል ጥያቄ፤ የሞት ሽረት ትንቅንቁ መለያ ስለሆነ በይሉኝታና በሽማግሌ ወይም በዕርቅ የሚፈታ አይደለም:: በበኩላችን ዛሬ ሳይሆን በ1983 ገና ወያኔ ስልጣን ሻይዝ ይህ አገዛዝ በሁለ ገብ ትግል መወገድ አለበት ብለን ስለነበር ዛሬ ይህን በተመለከተ የምናርመው ብዥታ የለም:: ሊከሰት በጣረበትም ታግለን አችንፈነዋል:: በህዝብና በወያኔ መሀል አሸናፊና ተሸናፊ መኖር አለበት:: ሕዝብን በፊጀ አገዛዝ ላይ ቂም የለንም የሚሉቱ ከሚቾቹ ወገን--ዘመድ ጋር መነጋገር ሊኖርባቸው ነው:: ከዚህ አንፃር በደቡብ አፍሪቃ ዕርቅና ሰላም ወረደ ማለቱም አያስኬድም፤ ሀቅ ካለመሆኑ ሌላ ጋሪውን ከፈረሱ ያስቀድማል:: አገዛዙ ከወደቀ በኋላማ የትኛው መፍትሄ ይበጃል ብሎ መወሰኑ ሌላ ነው:: መጀመሪያ ግን አገዛዙ መወገድ አለበት:: መውደቅ መንኮታኮት:: ይህን የሚፃረርና የመለስን አገዛዝ ዕድሜ እናራዝም የሚል ባዕድ መኖሩ አይገርምም--መለስ ዜናዊ የባዕድ ተገዢ ነውና:: ይህን የሚል ሀገር- በቀል ሀይል ወይም ቡድን መኖሩና ራሱን ደግሞ ተለጣፊ ሳይሆን ተቃዋሚ ሊል መጣሩን ግን በዝምታ የምናልፈው አይሆንም::

ጉድጓዱ በወያኔ ራሱ ከተማሰ ዓመታት አልፈዋል:: በዚህ በኩል ጭቁኑ ሀገር ወዳድ ህዝብ አለ:: በወዲያ በኩል ደግሞ ወያኔና ያወቁም ያላወቁም ጭፍሮቹ አሉ:: ድልድይ የለም:: ቅራኔው ወሳኝ ነው፤የማይታረቅ ነው:: መፍትሄው የሚገኘው በትግልና በትግሉ ውጤት ብቻ ነው:: በወያኔ ፓርላማ የሚገኝ መፍትሄ የለም:: በባዕድ አጋፋሪነት የሚገኝም የለም:: ጠላትን ወዳጅ ብሎ በመለፈፍም የሚገኝ ስርየት ሳይሆን የከፋ ባርነት ነው:: ለዚህም ነው ቢያስረንም ቢፈጅንም አንጠላውም የሚለው ዲስኩር ለእኔ ብጤውና ለህዝብ አልገባ የሚለው:: መጥላት ይነሰን እንዴ! ጠላት ወዳጅ ሳይሆን አልለማመጥም ብለዋል የጥንት ኢትዮጵያውያን:: ዛሬ ሰላማዊ ትግል ብቻ የሚባለው ግደለን አንጠላህም ፖለቲካ፤ በጠላት ላይ አለማክረር፤ ቢበድሉንም አንጠላቸውም ወዘተ በሚል ተራቀቀ ተብሎ የሚስተጋባው ፖለቲካ ታሪካዊ ማጠየቂያ የሌለው ነው:: የአረመኔውን አገዛዝ ፀረ ህዝብነት አለዝቦ ማቅረብ ሳይሆን አጋልጦ ለአመረረ ትግል ጥሪ በማድረግ ፈንታ ያደረገውን ላወቀ አገዛዝ ኤሎሄ ኤሎሄ ያደረገውን አያውቅምና ይቅር ብለናሉ መጨረሻው የባርነትን ቀንበር ተሸክሞ መቀጠል ነው:: ይህ ደግሞ በህገራችን ታሪክ ማጠየቂያ ሲያጣ ወደ ህንድና ጋንዲ ቢወነጨፍም በዚያም ሆነ በሌሎች ሀገር በዚህ ዘዴ የተገኘ ነፃነት የለም:: ህንድ ነፃነቷን የተጎናፀፈችው በጋንዲ ሰላማዊ ትግል ሳይሆን በአመፅና በወቅቱ በተከሰቱ የተወሳሰቡ የፖለቲካ ችግሮችና ገጠመኞች ነው:: ይህ የተስፋፋ አመፅ ጋንዲን በጣም ሰላበሳጨው በህንድ የነፃነት ቀን በዓል ላይ ለአለመገኘት መወሰኑና አለመገኘቱ በታሪክ የተመዘገበ ነው:: ደቡብ አፍሪካ፤ ፍልስጤም፤ የአፍሪካ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል፤ ደቡብ ሱዳን፤ ዳርፉር፤ በእስያ ወዘተ ጠላትን ወዳጅ ያለ አልነበረም፤አይደለም:: አመፅን የሸሸ ትግል ውጤት አላስገኘም:: ትላንትም ዛሬም ያለው ሀቅ ይህ ነው:: ከዚህ ሌላ ደግሞ ሰላማዊ ትግል በተባለበትም (በቅርቡና በሰሞኑ በርማ ወይም ሚያንማር የተባለውን የእስያ ሀገርና በዚያ የሚካሄደውን ትግል እንደ ምሳሌ ብንወስድ) ፀረ አገዛዙ ትግል መካሄዱ የግድ ሆኖ ሲካሄድና መስዋዕትነትም ሲከፈል ታየ እንጂ ከጠላት ጋር በመደራደር ብቻ መፍትሄ ሊገኝ ሲሞከር አልታየም:: በሀገራችንም ቢሆን ባለፈው የግንቦት ምርጫ የተካሄደው ትግል ያስገኛቸው ውጤቶች ከወያኔ መፋለምን ያቀፉ እንጂ ተለጣፊነትን ያስቀደሙ አልነበሩም:: ይህን ሀቅ ብንናገር ታዲያ ምነዋ ውግዘቱና ክሱ ተበራከተ ?

በጣዖት ማመኑ አልዋጥ ያለን ደግሞ መሪዎቻችን ነን በሚሉንም (ያውም ሳንመርጣቸው ብዙውን ጊዜ) ላይ ቢሆን መሳቅና "መቀለድ" መብታችን ነው ባይ ነን:: ከመቶ አለቃ ግርማ እስከ ብርቱካን ሚዲቅሳ ወደ አሜሪካ ተጉዘው የቴክስ ወይም የካውቦይ ወይም የአሜሪካ እረኛ ቆብ አጥልቀው ዳንሱንም በአደባባይ ሲያቀልጡት ስናይ "ቴክሱ ፈረሰኛ አሸዋ ላይ ተኛ" ማለቱ ቢመጣብን ምን አለበት? ይህን ቆብ አድርገው ያየናቸው እነ ስመ ጥፉ ሮናልድ ሬጋንና ጆርጅ ቡሽ (አባትና ልጅ) በመሆናቸው ሀበሾቹ ማለትም የአገዛዙ ሹመኛና ተቃዋሚ የተባሉት ሁሉ ይህን የሰዎቹን የባህል ወይም "ሀገራዊ" ቆብ አጥልቀው ሲገኙ መተቸት ወይም "መፎተት" በወለፈንዲ መቸም የሚያስቆጣ አይሆንም:: ከወደ ሀገር ባህሉም ተመሳሳይ የሚታይ ነበርን እንዳንል ምንም እንኳን ተቃዋሚዎቹ የሀገር ባህል ልብስ አድርገው ባላይም መለስ ዜናዊም የሀገር ልብስ ለብሶ በሚሊኒየሙ በዓል ፎቶ መነሳቱን ማየታችን አልቀረም:: ጨርቅ ያላትን ሰንደቅ ዓላማችንንም የሚያከብር መስሎ መታየት ጀምሮ የለ ? በዚህም በዚያም ግን ይህ ሁሉ የላይ ላይና ሁላችንንም የሚመለከት ነው:: ብንስቅባቸው አይቆጡ ለማለት:: ቴክሱ ባለቆብ የሆነው የአሜሪካ ሎሌ ሆነ ማለት እንዳልሆነው ሁሉ የሀገር ልብስ እየለበሰ ቀይ ሽብርና የሰኔ 97ም ግድያን ያካሄደውን እናውቃለን:: የሀገር ልብስ የሚያዘውትሩ አዛውንት በአስታራቂ ስም "እጅ አስነሺ" ሆነውም ታዝበናል:: የሀበሻ ቴከሶቹ ጉዳይ ቢያስቀን ግን ልንስቅባቸው መብት እንዳለን ባይካድ ነው ዋናው ነጥቡ:: የፖለቲካ መሪዎችን ልናከብራቸው የምንችለው በስራቸው ሲሆን በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ደግሞ ተመራጮቻችን ወይ አገልጋዮቻችን ናቸውና ልንተቻቸውና በተለምዶው አነጋገር ልንሸረድዳቸውም መብታችን የተከበረ ነው:: ልንሰግድላቸው ሳይሆን:: ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ የሰለጠነ ፖለቲካ አይደለም::

የወያኔ ፕሬዚዳንት ስምሪት ባይመለከተንም የተቃዋሚ መሪዎች ግን ከእስር ሲወጡ ወደ ገጠሩ ሄደው፣ የባላገሩን የሰሌን ቆብ አጥልቀው፣ ለህዝቡ ስለ ምህረት ጥየቃውም ሆነ ስለ መጪው መራራ ትግል ገለፃ ቢሰጡ ማየቱ ይበልጥ ደስ ባለን ነበር:: ሻምፓኙ ቀርቶ ኮረፌውን ደጋውን ቢጎነጩ :: ይያዙ ብሎ ነበር የተባለውን የአሜሪካንን አስተዳደር ከማመስገን ይልቅ ህይወቱን የሰጠላቸውን ህዝብ ማመስገኑን ቢያስቀድሙ ይበልጥ ባረካን ነበር:: የቴክሱ ቆብ ቧልትነት ይዘቱ እዚህ ላይ ነው:: ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ፖለቲካ :: ቆዳ ጥቁር ጨምበሉ ነጭ:: ሕዝብና ሀገርን ማስቀደሙ ሲያቅት ፖለቲካው ሰለጠንኩ እያለ ማጥ እየገባ የነፃነታችን ቀነ ቀጠሮ ተራዘመ ::

የሚፈለግ ተኖ መሆን የሌለበት ሆኖ ሲመጣ
ሁሌም ባይሆን ኖሮ ባልነበር ጫጫታ

ነውና ድርጅቶች ባይከፋፋሉ ኖሮ ምንኛ ደስ ባለን ነበር:: ህብረቱ በተቋቋመ በነጋታው ባይከፈል፣ ቅንጅት እንደሰመረ ቢቀጥል ኖሮ፣ ህብረትና ቅንጅት ሰምረው በነበር፣ በ 66 ኢሕአፓ ና መኢሶን ባልተጣሉ ኖሮ ወዘተ ወዘተ:: ገፋ ካደረግነው ደግሞ ወያኔ ወያኔ ባልሆነ ኖሮ እያልን መጓዝ፣ ማለም፣ መቆጨት እንችላላን:: ኑሮ ግን በኖሮ በነበረ አይኖርም:: ወደድንም ጠላንም የተከሰተውን ማየት፣ማወቅ፣መቀበል አለብን:: ድርጅቶች የህብረተሰቡ ቅራኔ ነፀብራቅና ውጤት ናቸውና ህብረሰቡን ከሚንጡት ቅራኔዎች ውጪ ሊሆኑ አይችሉም:: ስለዚህም ቅራኔዎች መከሰታቸው አይቀርም:: ምን ዓይነት ቅራኔ? እንዴትስ መያዝ ይገባል?

ለሚለው የሚሰጠው ምላሽ ነው ፖለቲካ ብልህነትን የሚያመለክትው:: የድርጅቶች ልክና ችሎታም በዚሁ ሊገመት ይችላል:: ከዚህ ባሻገር ግን አብረው ሊሰሩና ሊሄዱ የማይችሉ ድርጅቶች መለያያታቸው የግድ ነው:: ለትግሉም የሚጎዳ ሳይሆን ይጠቅማል:: በህዝብ ጎራ የሚመደቡ እስከሆነ ድረስ አለመጋጨታቸው ደግ ሲሆን በግድ ግን ስሙሩ ማለቱ የሚያስኬድም የሚጠቅምም አይሆንም:: ኢሕአፓና መኢሶንን ብንወስድ በመስመር ልዩነት ቀደም ብለው ቢለያዩም ወደ ከረረው ጠብ በችኮላ ዘው አላሉም:: በአዲስ አባባ ከተማ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ኢሕአፓን ወክሎ ዶክተር ሀይሌ ፊዳ ደግሞ መኢሶንን ወክሎ ውይይቶች ተካሂደው ነበር:: ድርጅቶቹ የነበራቸው የፖለቲካ አቅዋም የሚጣጣም ባለመሆኑ ሊስማሙ አልቻሉም:: በመኢሶን በኩል ለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ሂሳዊ ድጋፍ ሰጥትን አብረነው እንስራ የሚል መስመር ሲኖር በኢሕአፓ በኩል ደግሞ ይህ መንግስት ፈርሶ ደርግንም ያካተተ ቢሆን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም የሚል ነበር:: ትላንት በህብረቱ መሀል ወያኔ ፓርላማ እንግባና አንግባ በሚለው የተከሰተው ልዩነት ሊጣጣም የሚችል አልነበረም:: ዛሬ በቅንጅት ውስጥ ያለው ልዩነት ይህን ይመስላልን? መልሱን ለታዛቢዎች የምተወው ሲሆን ያሉትን ችግሮችና እውነታዎች አንስቶ የተቸውን የእንጦጦ መምህር ቢናገር በዓመት ያውም ሬት ዓይነት ማብጠልጠሉ ከቶም ትክክል አይደለም:: ያውም ችግሩ ምስጢር ሊሆን ቀርቶ በየአዳባባዩ ተሰጥቶ ወያኔ ራሱ እጅ እጅ አለኝ እያለ እየቀለደበትና እየቀለደብን ሳለ "ግራዝማች ቸኮል ልብሱ አልቀበት/እርቃኑ ስጋውን ሲሄድ አየሁት/ ያለውን ግለሰብ በአደባባይ የሚታየውን አጋለጠን ብሎ ማውገዙ የሚበጅ አይሆንም:: በኖሮ መኖር ካለመቻሉ ሌላ የሰጎን ፖለቲካ ደግሞ፤ ያለን ችግርና ቀውስ አላይም ብሎ የመጨከኑ ፖለቲካ የሚያስከትለው ውድቀትን ነው::

በድርጅቶች መሀል የሚነሱ ችግሮችን በአግባቡ ለመፍታት መጣሩ ጠቃሚ ነው:: አንዳንድ የፖለቲካ ዕይታቸው ሸውረር ያለ ክፍሎች በድርጅታዊ ትምክህት ተይዘው ለብቻችን ብቻችንን ለሁሉም መፍትሄ እንሰጣለን፤ለድል እንበቃለን ብለው የተሳሳተ ድምዳሜ ቢደርሱም ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ማበባቸውና ህልው ሆነው መገኘታቸው ለትግሉም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ አስፈላጊ ነው:: ስለሆንም ቢያንስ እኔ/እኛ የሆነ የህዝብ ድርጅትን መክሰም ወይም መድረኩ በአንድ ድርጅት ብቻ መያዝ ወይም በሀገሪቷ ከሁለት ሶስት በላይ ድርጅት መኖር የለበትም ብለ ወመሰንን የምንቀበለው አይደለም:: ስለሆነም ትችታችን ከመነሻው ጀምሮ ገንቢ ነው:: በእርግጥ በትችትና ሂስ ሽፋን፤ ድርጅትን መከርን ገነባን እያሉ ሊያፈርሱ አቅደው ደርማሽ፤ አፍራሽና በታች ዘመቻ የሚያካሂዱ ነበሩ፤አሁንም አሉ:: እነዚህን ሁሉ ድርጅት መታገል አለበት እንጂ ገንቢ ሂስና ቀና ምክር ሊሰጡ የሚጥሩትን ሁሉ ከመ እንጦጦ መምህር ማውገዙ ስህተት ይሆናል:: ከነባር ድርጀቶች ተመክሮ መማር ድክመት ሳይሆን ብልህነት ነው:: ታሪክን አክቾልችሎ የሚነሳና ያለፈውን የዘነጋ ስህተትን ይደግማል እንጂ ውጤታማ አይሆንም:: አዛኝ ቅቤ አንጓች እንዲሉ ለድርጅቶች የተቆረቆሩ መስለው የድርጅቶችን አስተዋፅዖና ሚና ረጋግጠው፤ ታሪክን ከልሰውና ቀልብሰው ሽንፈትና ጨለምተኛነትን እያሰፈኑ ክፍፍል የሚያባብሱና የትግልን ስሜት የሚገድሉ አሉ:: በተወሰኑ መድረኮች ላይ በየማታው ሲለፍፉ እንደምንሰማውና መገመት እንደምንችለው ብዙዎቹ ለወያኔ ወይም ለባዕድ ያደሩ ሳይሆኑ አይቀሩም ቢባል የተሳሳተ አይሆንም:: ከእነዚህ መሰሪዎች መጠንቀቁ ሲገባ ገንቢ ሂስን ግን መጋበዝና በቀና መቀበልም ይጠቅማል::

ይህን ስንል ትችቱ ሚዛናዊ ይሁን ማለት ደግሞ አግባብ ያለው ነው:: ባለፈው የግንቦት ምርጫ በተቃዋሚዎች በኩል የነበሩ ብዥታዎችና ስህተቶች እንዳሉ ሆነው የተቃዋሚ ድርጅቶችና የህዝብ ትግል ያስገኘውን ድል (ምንም እንኳን የተፈለገው የመጨረሻው ድል ባይሆንም) መካድ አይገባም:: በዚህም መልክ መሪዎችም ያደረጉትን አስተዋፅዖ በአግባብ ማየት እንጂ በጅምላ መኮነኑ ጠቃሚ አይደለም:: ከዚህ ሌላ ግን የሰዎች ጣዖቶች ቀርፀናል ለሚሉ መልሳችን በዚህ አምልኮተ ባዕድ አንሰማራም የሚል ነው:: ከስህተታችን ማማሩ ለመጪው ትግልና ዕቅድ አስፈላጊ ነው::

ለመደምደም--አሁንም እንደገና ከቃለአጋኖና አፍራሽ ፖለቲካ መራቅ፣ ለጠላት እጅ መስጠት የሰለጠነ ፖለቲካ አለመሆኑን መቀበል፣ ክፍፍልን ለማስወገድ በቀና ልብ መነሳት፣ ለህዝብ የተገባውን ቃል ኪዳን ማክበርና አምርሮ ወያኔን መታገል ያስፈልጋል:: መልዕክቱ ከመረረ መልዕክተኛውን መግደሉ መፍትሄ አይደለም::

ሀቅን መቀበል አንፍራ!!
በተባባረ ትግል ጠላትን እናቸንፍ!!
ድል የጭቁኑ ህዝብ ናት!!